# አንድነት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር

**ANDINET NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT ORGANIZATIONS (KNAASO)**

766 Rock Creek Church Rd. NW. Washington DC. 20010
Tel: (202) 541 0556 Fax: (202) 541-0557 Email: kinijit@kinijitnorthamerica.org


ኦገስት 24 2008 ዓ/ም

## አንድነት ፓርቲ በአዲስ ምዕራፍ ይጀምራል!

**አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ** ሕጋዊ ሰውነቱን ያገኘው ሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ረሃብ፤ የኤኮኖሚ ድቀትና የፖለቲካ አፈና የሕዝቡን መንፈስ ክፉኛ ባጎሳቀሉበት ወቅት እንደሆነ በውል እንገነዘባለን። በተቃዋሚው ረድፍ የሚታየው ውዝግብና ተቻችሎ ለመሥራት አለመቻልም ሌላው ብሔራዊ ፈተናችን መሆኑን እናውቃለን።

በንዲህ ዓይነቱ ወቅትና በንደዚህ ያለ ሁኔታ የአንድነት ፓርቲ በገሃድ መንቀሳቀስ መቻል ተዳፍኖና ተጠፍሮ የነበረው ያገራችን ፖለቲካ አዲስ ሕይወትና አዲስ ጉልበት አግኝቶ እንዲራመድ በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ከዚህም በተጨማሪ የአንድነት ፓርቲ እውን መሆን የቀድሞው ቅንጅት በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ፈጥሮት የነበረው የተስፋ ዘመን እንደገና እንዲያብብ ስለሚያደርግ ታላቅ ቁምነገርን አዝሏል።

የፓርቲው መጠሪያ ሥም ሕዝባችን **ለአንድነት፤ ለዴሞክራሲና ለፍትህ** እየከፈለ ያለውን መስዋዕትነት የሚያመላክት ነው። የነዚህ ክቡር ፀጋዎች እውን መሆንም ለህልውናውና ለብሩህ ተስፋው ወሳኝ ግብዓት እንደሆነ የሚያሳስብ ነው።

ፈታኝ በሆነው በዚህ የታሪክ ዘመናችን አንጓ ላይ የፓርቲውንና የሕዝባችንን ቀንበር ለመሸከም ፈቃደኛ ከሆኑት መሪዎች ብዙ እንደሚጠበቅባቸው እናውቃለን። አስተዋይነት፤ ሆደ ሰፊነት፤ የዓላማ ጽናት፤ በሕዝብ መታመን ዋና ኃይላቸው እንደሚሆኑ ላንዳፍታም አንጠራጠር። የሀገራችን የፖለቲካ ይዘት ከቀድሞው ውጥንቅጥና ኋላቀር ባህርይው ፀድቶ ያዲሱ ዘመን የፖለቲካ ድባብ አካል እንዲሆን በሚደረገው ጥረት ውስጥ ፊር-ቀዳጅ ሚና እንደሚጫወቱ እናውቃለን። የኢትዮጵያ ትንሳዔ በሁሉም ልጆቿ ተሳትፎ የሚገኝ ስለሆነ የተለያዩ አመለካከቶችን ሊያቀራርቡ የሚችሉ ድልድዮች መሥራት አንድ አቢይ ተግባራቸው እንደሚሆን ያረጋገጥነው ጉዳይ ነው።

አንድነት ፓርቲ ያሳለፋቸው ሁለትና ሦስት አመታት በዋጋ የማይተመን ጥቅጥቅ ያለ ትምህርት አጎናጽፈውት አልፈዋል። ዛሬ ሥራውን የሚጀምረው እነዚህን ትምህርቶችና ተመክሮዎች ምርኩዝ አድርጎ ስለሆነ ለውጤታማነቱ ጥርጥሬ አይኖረንም። እስርና እንግልት አንድነትን ይበልጥ ብልህ፤ ይበልጥ ጠንካራና ይበልጥ ንቁ አደረጉት እንጅ አንዳንዶች እንደሚመኙት አላዳከሙትም።

በሚሊዮን የምንቆጠር የቀድሞው ቅንጅት ያሁኑ አንድነት ፓርቲ ደጋፊዎች ትናንትም ዛሬም ያነገብነው የ "ይቻላል"ን መፈክር ነው። አዎን ዴሞክራሲ ይቻላል! አዎን አንድነት ይቻላል!

አዎን ስልጡን ፖለቲካ ይቻላል! አዎን ሕዝብ በሠላማዊ ትግል መብቱን መጎናጸፍ ይችላል! አዎን በወንድማማች ሕዝቦች መሀከል እርቅና ሠላም ይቻላል! አዎን ኢትዮጵያ ሠላምና መረጋጋት የሰፈነባት የከበረችና የተከበረች አገር ትሆናለች! እንላለን።

የዴሞክራሲ ትግሉ ከምንጊዜም በረቀቀ ስልትና በተሀድሶ ብሔራዊ ስሜት እንዲቀጥል ለአንድነት ፓርቲ የሚያስፈልገውን ድጋፍ ሁሉ እንደምንሰጥ በዚህ አጋጣሚ ቃል ኪዳናችንን እናድሳለን። አሻግረን የምናየው ብሩህ ተስፋ መሆኑን ብናውቅም ብዙ መሰናክሎችና ብዙ ፈተናዎች ማለፍ እንዳለብን እንገነዘባለንና በደስታውም በችግሩም ጊዜ መንፈሳችንን ጽኑ አድርገን ከፓርቲው ጎን እንደምንቆም እናረጋግጣለን። በዚህ አጋጣሚ መላ ወገናችንን እንኳን ደስ ያላችሁ እንላለን።

**የኢትዮጵያ ትንሳኤ ይቻላል!**
**ረጅም ዕድሜ ለአንድነት ፓርቲ!**
**ኢትዮጵያ ለዘልዓለም ትኑር!**